# ኢሳት ጥቁሩን ሂትለር = ፋሺስት ማስተናገድ ነበረበት እንዴ?

ሲራክ ከሚድዌስት

 

ሁለት ፎቶዎች ይታዩኛል፡፡ ሁለቱም ሂትለር ናቸው፡፡ በርግጥ አንዱ ጥቁር ነው አንዱ ደግሞ ነጭ፡፡ እንዴት ነው አይኔ ሁለት ያውም ጥቁሩ መንግስቱ ነጩ ሂትለር መሆናቸውን እያየ አእምሮዬ ሁለቱንም አንድ አድርጎ የወሰነው? ምናልባት ሁለቱም ተመሳሳይ ክፉ ገጸ-ባሕሪያት ስላላቸው ይሆን? ጥቁሩ ሂትለር በሰው ማጥፋት ወንጀል ተፈላጊ ነው፡፡ እንኳን ጥቁሩ ሂትለር የበታች የበታች የበታች ግልገል ፋሽስቶቹ ዛሬ ከምደረ አሜሪካ በመመንጠር እየተለቃቀሙ ስለመሆናቸው ማየት ታድለናል፡፡

ጀርመናዊው ሂትለር ጁሾችን ስለሚጠላ ድራሻቸውን ከምድ-ረገጽ ለማጥፋት በሚሊዮኖቹን  ጨፍጭፏል፡፡ ኢትዮጵያዊው መንግስቱ ለውጥ ፈላጊውን፡ አገር ወዳዱንና ብርቅዬ ኢሕ አፓዎችን ጠልቷል፡፡ ድምጥማጣቸውን ከምድረ ገጽ ለማጥፋት በቀይሽብር ዘመቻው ከግማሽ ሚሊዮን በላይ ንጹህ ደም ጠጥቷል፡፡ ሁለቱም ፋሽስት ናቸው፡፡ አንደኛው ሆሎኮስትን የኛው ደግሞ ቀይ-ሽብርን ያስታውሱናል፡፡

ሁለቱም ተወዳዳሪ ያልተገኘላቸው አምባገነን፤ትምክህተኞች፤ካለነሱ ሃሳብ በስተቀር የሌላውን የማይቀበሉ፤ ኢሰብአዊ የሆኑ ሲሆኑ ሁለቱም በየራሳቸው መንገድ ራስ ወዳድ ናቸው፡፡ ያለኔ በስተቀር ማንም አይነካኝም ያለው ነጩ ሂትለር ራሱን በራሱ አጠፋ፡፡ እንደ ቴድሮስ አንድ ጥይት ለራሴ ይል የነበረው ጥቁሩ ሂትለር ሕይወቱን ለማትረፍ ወደ ሃራሬ ኮበለለ አገሩን ለጠላት አጋልጦ፡፡

ነጩ ሂትለር በሰው ዘር ላይ ባደረሰው ፍጅት የተነሳ የራሱ ሕዝብ አንቅሮ ተፍቶታል፡፡ በርግጥ ጥቂት መሰል አላማ ያላቸው ጥቂት አምላኪዎች ብቅ ብቅ ቢሉ አያስገርምም፡፡ በቀይ ሽብር ከግማሽ ሚሊዮን በላይ ሕዝብ የፈጀው፤ በእኩይ አመራሩ ሰራዊቱን በታትኖ አገርን ለአገር አጥፊው ወያኔና ሻቢያ አሳልፎ የፈረጠጠው ጥቁሩ ሂትለር የመላው ኢትዮጵያ ጥላቻን ያተረፈ ሲሆን ጥቂት ወዳጆች ቢኖሩት መደነቅ አይገባንም፡፡ጥቁሩ ሂትለር በኢሳት ቲቪ ቃለ-መጥይቅ ተደረገለት፡፡ከጥቂቶቹ አድናቂዎቹ አንዱ ኢሳት ቴሌቪዥን መሆኑ ይሆን? የሚመስለው እንጂ የማይመስለው አልታየም፡፡

አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን በወያኔ ላይ ያነጣጠርነውን ጦር ሳናላላ ስለ ኢሳት ጉዞ ልብ እንድንል ማስገንዘብ እፈልጋለሁ፡፡ ሂትለር ዛሬ

በሕይወት ኑሮ ቢሆን በመታደን ላይ ነበር፡፡ ኢሳት ሃሰት አይለኝም፡፡ ጥቁሩ ፋሺስት መንግስቱ በሕዝብ ደም በኢትዮጵያውያን

ይፈለጋል፡፡ ምናልባት ኢሳት ይህን ሃቅ አያውቅም ይሆናልን?

ኢትዮጵያዊነት ይለምልም!

12/14/2013